# ነፍስ ይማር!

## የተስፋዬ ገብረአብ ጉዳይ ሲገመገም

ከ ነፃነት ይልማ

...........በየወቅቱ በተለያዩ ማህበራዊ ድህረ-ገፆች መነጋገሪያ ሆነው የሚያልፉና እጅጉን ሲያነጋግሩ የሚሰነብቱ ርዕሰ-ጉዳዮች መኖራቸው እሙን ነው። ሰሞኑን የሚዲያ ዳሰሳ ሳረግ የቃኘሁት ጉዳይ ግን፤ እኔንም ከተመልካችነት ወደ ተሳታፊነት አሸጋግሮኛል። ይህ መጣጥፍ በደራሲ ተስፋዬ ገብረአብ ምግባር ላይ ያተኮረ ነው።

ተስፋዬ ገብረአብ በወታደራዊው ደርግ አስተዳደር የሥልጣን ዘመን መጨረሻ ከውርሶ መኮንኖች ማሰልጠኛ ተቋም በምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግ ተመርቆ የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰራዊት ውስጥ ቢቀላቀልም የመንፈቅ ደሞዙን ሳይበላ በ1981 ዓ/ም ደብረታቦር ላይ በምርኮ ውስጥ በመውደቁ ፤ ከዚያን ግዜ ጀምሮ በቀድሞው የመከላከያ መኮንኖች በተመሰረተው ኢ.ዲ.መ.አ.ን (የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ መኮንኖች አብዮታዊ ንቅናቄ) በተሰኘ ድርጅት ውስጥ ተሳታፊ በመሆን በሚዲያው ዘርፍ በሬዲዮ አዘጋጅነት ሲያገለግል ቆይቶ ሳለ፤ ያለ ድርጅቱ ምንም አይነት እውቅና በኤርትራዊው የወያኔ ባለስልጣን በረከት ስሞን ድጋፍ ወደ ስልጣን ማቅናቱን በወቅቱ በቦታው ላይ የነበሩ የሥራ ባልደረቦቹ ይመሰክራሉ።

ተስፋዬ ገብረአብ ከልጅነት አምሮው ጀምሮ ኤርትራዊነቱን እያገዘፈ በማየት፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማፈራረስ በነበረው እቅድ በቀደምትነት የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል በመሆን አድፍጦ ከቆየ በኋላ፤ በምርኮኝነት ወያኔ ኢህአዴግን ተቀላቅሎ ከመረጃ ሥራ እስከ ፕሬስ መምሪያ ሀላፊነት ሲያገለግል ንፁሀን ኢትዮጵያውያንን ሲወጋና ሲያስወጋ ከርሞ፤ ዛሬ ደግሞ በስደቱ ዓለም ተቃዋሚውን ጎራ በመምሰል የበግ ለምድ ለብሶ በባለ ሁለት ስለታማ ካራ፤ በአንድ በኩል አሳዳሪው የነበረውን ወያኔን እየሸነቆረ፣ በሌላ በኩል የአንድነት ሀይላት የሆኑትን የተቃዋሚ ድርጅቶች እየገዘገዘ ለመጣልና በየአቅጣጫው የሚቀጣጠለውን የነጻነት ትግል ውጤት አልባ ለማድረግ ሌት ተቀን የሚሰራ ከመሆኑም ባሻገር፤ ከዚህ ቀደምም በደም ቀለም እየከተበ ያሰራጫቸው መጣጥፎቹ ታሪክን እያዛቡ፣ ቁርሾን እያማዘዙ፣ ወገን-ከወገን ከማፋጀት የዘለለ እርባና አልታየባቸውም።

የሻቢያ ጆሮ ጠቢ የሆነው አቶ ተስፋዬ ገብረአብ በኔዘርላንድ ውስጥ ሂልቨርሱም በምትባል ከተማ ለሁለት አመታት ያህል ተጠልሎ ሲኖርበት በነበረው ቤት ውስጥ ለዘመናት መርዝ ይረጭባቸው የነበሩ በእራሱ የእጅ ፅሁፍ የተፃፉ በፎቶ የተደገፉ በርካታ ሰነዶች አከማችቶ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆኑ መልእክቶችን እያሰራጨና ቅስቀሳዎችን እያደረገ ሲኖር፤ በባለቤትነት ባስጠጋው ወጣት አለማየሁ መሰለ ብርቱ ክትትልና ጥንቃቄ በተሞላበት የመረጃ አሰባሰብ በየግዜው እየተቀዱ ከእጁ ሾልከው ሊወጡ ችሏል። ከዚህ በመነሳት ሰሞኑን በመረጃ ተደግፎ በዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻ አቀናባሪነት ለአደባባይ የበቃው ባለ አርባ ሰስድስት ገፅ ፅሁፍ የተጋዳላይ ተስፋዬን ማንነትና ፀረ ኢትዮጵያዊነት አቋም ቁልጭ አድርጎ አሳይቶናል። ሙሉ ፅሁፉን በ (www. ethiomedia.com) ወይም (www.ethiopatriots.com) ይመልከቱ።

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ እንዳስተዋልኩት ከተስፋዬ መረጃዎች በመነሳት ብዙ ማለት ቢቻለኝም ሁለት ነገሮች ላይ ሃሳቤን አስፍሬ ማለፍ እፈልጋለው።

1- ከቀረበው መረጃ እንደምንገነዘበው ከሆነ ፀሀፊ ተስፋዬ ገብረአብ ዛሬ በስልጣን ላይ ያለውን የወያኔን መንግስት ጉድፍ በብዕሩ አጉልቶ እሚያሳየን በመምሰል፤ በለሌላ በኩል የተቃዋሚውን ጎራ እርስ በርስ በማናቆርና፤ በተለይም ብሄርን ከብሄር በማጋጨት፤ ያደገባትን፣ የበላባትንና ወግ ማእረግ ያሳየችውን <u>ውድ</u> <u>እናት ሀገራችንን ኢትዮጵያን</u> ማፈራረስ አንዱና ቀዳሚ እቅዱ እንደነበረ እናያለን። ተስፋዬ እንኳንስ አሁን በስደቱ ዓለም በርካታ ፀረ-ወያኔና ፀረ-ሻቢያ የሆነውን ኢቲዮጵያዊ ተቀላቅሎና ቀድሞም በዘመነ ወያኔነቱ <u>ሥጋው አዲስ አበባ መንፈሱ አሥመራ</u> እንደነበረ እንገነዘባለን። በዚህ አጋጣሚ የሻቢያ የተስፋ ልጅ የሆነው ተስፋዬ ገብረአብ ማንነቱና መጥፎ ምግባሩ አደባባይ መሰጣት ጥቂት የማይባሉ ወያኔዎችንና አፍቃሪ-ወያኔዎችን ያስፈነደቀ ሲሆን፤ እነዚሁ ወያኔዎች የተፈጠረውን አጋጣሚ በመጠቀም በኢትዮጵያዊነት ስም ሊወዳጁን ሲሞክሩ ለማስተዋል ችለናል። ዳሩግን ወያኔም ሆነ ሻቢያ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶችና የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች መሆናቸን ሊያውቁት ይገባል!!!

2- በዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻ ከሰፈረው አስተያየትና ከባለ ታሪኩ አቦይ ተስፋዬ የእጅ ፅሁፍ እንደምንገነዘበው በአውሮፓም ሆነ በመላው ዓለም በተበተነው በረካታ ኢትያዊ ስደተኛ መሀል እንደ ትንታግ የምናያቸው፣ ትግሉን የሚያቀጣጥሉ፤፣ ለወያኔና

ለሻቢያ የእግር እሳት የሆኑ፣ ሌት ተቀን ጉልበታቸውን፣ ገንዘባቸውንና፣ ግዜያቸውን፣ ከዚያም በላይ ሒወታቸውን የሰጡ ብርቅዬ ዜጎችን ውሎና የቤታቸውን ጓዳ መሰለል የተስፋዬ የእለት በዕለት ሥራው ሲሆን፤ አላማውም ግለሰቦቹን አግባብቶ በጠላት ቀለበት ውስጥ ማስገባት፣ ካልሆነም ከትግሉ ሜዳ አሽቀንጥሮ ማውጣት ነው። ለዚህ እኩይ አላማው ደግሞ እንደ ክንፉ አሰፋ ያሉ አላማቸው እጅግ ያልታወቀ ሰዎችን በእጁ ይዞ እንደሚንቀሳቀስ ከተሰራጨው ባለ 46 ገፅ ፅሁፍ እንዲህ እንረዳለን፦ (........**ተስፍሽ አመቺ ከሆነለት የአውሮፓ ሀገሮች ስዊድን፣ ጀርመን፣ ከሚኖርበት ሆላንድና ቤልጅየም፣ አመቺ ሰዎችን በማግኘት እንዳለው የሚፈልገውን ቦርቡሯል። ለነገሩ ሆላንድ ችግር ያለበት አይመስለኝም። ጋዜጠኛ ክንፉን እንደማይነቃነቅ ግንብ አድርጎ ይዞታል። እናም ክንፉም በጣም ተመችቶታል። ሌንጮም በቀላሉ እጁ ወድቆለታል።የአማራውን ማህበረሰብ ከኦሮሞው ጋር ማጋጨቱንና ኢትዮጵያ ተበታትና እንድጠፋ ለጀመረው፣ እና ለቀጠለበት ሩጫ ምናልባትም ከሌንጮ አንዳች መጠምዘዥያ አግኝቶ ሊሆን ይችላል። ከዘረዘራቸው ሀገሮችም እንደዚሁ ስሜተኞች የሚያጣ አይመስለኝም።**........) ሲል ይቀጥላል። በዚህ አጋጣሚ ክንፉ አሰፋ የተስፋዬ ገብረአብን ታሪክ የሚያወሳው ፅሁፍ በሚዲያ መለቀቁ ስላስቆጣው ትልቅ አንባጓሮ ወስጥ እንዳለ ለመገንዘብ ተችሏል። በሌላ በኩል ይሄ ጉዳይ እጅጉን ያስቆጣቸው ኢትዮጵያኖች የሻቢያው መረጃ ሰው ተስፋዬ ገብረአብ አንድና ብቸኛ ወዳጅ የሆነው ክንፉ አሰፋ በሆላንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሊጠየቅበት የሚገባ ብዙ ጉዳዮች በመኖራቸው እርሱም ላይ ሊተኮርበት ይገባል ባዮች ናቸው።

በስተመጨረሻ ይህንን የተስፋዬ ገብረአብ ጉዳይ በተመለከተ ዋናው የመረጃ ሰብሳቢ የሆነው አለማየው መሰለ ሰሞኑን ላስቬጋስ ከሚገኘው የህብር ሬዲዮ ጋር ባደረገው ቃለ-ምልልስ ሲያስቀምጥ (.........**ይህ በመረጃ የተደገፈው የተስፋዬ ገብረአብ ታሪክ የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን፤ ታሪኩም ከውቅያኖስ ውስጥ በጭልፋ የተቀዳ ያህል ነው። ከዚህ በኋላም በመረጃ የተደገፉ ተከታታይነት ያላቸው ፅሁፎችን፣ ከተለያዩ አካሎች ጋር ያደረጋቸውን ግንኙነቶችን፣ በየትኛው ወቅት ከነማን ጋር ወዘተ የሚሉትን ሁሉ አግባብነታቸው እየመዘንን እናወጣለን**.........) ሲል ተደምጧል። ሊደነቅ የሚገባው ተግባር ነው።

*ለማጠቃልያ፦ ለዚህ ሁለት አመት የፈጀ ክትትልና በመረጃ የተደገፈ ሥራ የሳላዩ ሰላይ የሆነውን አለማየሁ መሰለንና ፅሁፉን በሚገባ አቀናብረው ለንባብ ያበቁትን ዳኛ ወለልደሚካኤል መሸሻን እያመሰገንኩ፤ ለዘመናት በጉያችን ተቀምጦ "ምግብ የጋራ ፖለቲካ የግል" በማለት ሌማታችንን ወና ያስቀረውን የትናንቱ ኢትዮ-ወያኔ የዛሬው ኤርትራዊ-ሻቢያ የሆነውን ታጋይ ተስፋዬ ገብረ-እባብን ነብስ ይማር! እላለው። ዳግም አይነሳምና!

16/10/2013

ሀገራችን ኢትዮጵያን ፈጣሪ በቸርነቱ ይጠብቅልን!